# በ2002 ሃገራዊ ምርጫ የተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ ለማስተናገድ የወጣ ቴክኒካል መስፈርት

I. ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያስተላልፉት ምርጫ ነክ መልእክቶች በራሳቸው አስቀርፀው ወይም ሙሉ ኘሮዳክሽኑን አሰርተው የሚያመጡ ከሆነ የብሮድካስት ስታንዳርድ የጠበቁ መሳሪያዎችና ፎርማቶች መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በቴሌቪዥን የሚተላለፉ የምርጫ መልእክቶች ተቀርፀው መቅረብ ያለባቸው በDV Cam እና በDVC Pro ካሴቶች ብቻ ነው፡፡ ማንኛውም ፓርቲ በነዚህ ፎርማቶች ማቅረብ ካልቻለ ለጥራቱ መጉደል ኃላፊነቱን ወስዶ በMin DV ማቅረብ ይችላል፡፡
- በሬዲዮ የሚተላለፉ የምርጫ መልዕክቶች የብሮድካስቲንግ ስታንዳርድ በጠበቁ CD እና DVD የተቀረፀ መሆን አለባቸው፡፡
- ፓርቲዎች በራሳቸው አስቀርፀው ወይም አሰርተው የሚያመጧቸው የምርጫ መልእክት የያዙ ካሴቶች መለያ ቁጥር፣ የፓርቲው ማህተም ሊኖራቸው ይገባል፡፡

II. ከላይ በተገለፀው አግባብ ማቅረብ ለማይችሉ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የስቱዲዮ ቀረፃ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ነው፡፡

2.1. ፓርቲዎች የሚያስተላልፉት የምርጫ ነክ መልእክቶች በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ስቱዲዮ ማስቀረፅ ከፈለጉ

- በንባብ የሚቀርበው የምርጫ ነክ መልእክት የያዘው ፅሑፍ በያንዳንዱ ገፁ የፓርቲው ማህተም ያረፉበት መሆን አለበት፡፡
- ፓርቲው በእያንዳንዱ የተደበለት የአየር ሰዓት የምርጫ ነክ መልእክቱን እንዲያነብለት የወከለውን ግለሰብ ሙሉ ስም፣ የምርጫ መልእክቱ የሚተላለፍበት ቀን የሚገልፅ መሸኛ ደብዳቤ አያይዞ መላክ ይኖርበታል፡፡
- ለምርጫ ቅስቀሳ የሚያስፈልጉትን የፓርቲው አርማ፣ የመወዳደሪያ ምልክት ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- በንባብ የሚቀርበው የምርጫ ነክ መልእክት በነፃ አየር ድልድል ከተሰጠው ጊዜ አለመብለጡን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

1.5/503